# ግብርና ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት በ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ላይ የተሰጠ ግብረ-መልስ

1. መግቢያ

የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት በኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀፅ 17 እና በውሳኔ ቁጥር 3/2014 አንቀፅ 29 በተሰጠው ሃላፊነት መሠረት የአስፈፃሚ አካላትን አፈፃፀም ይመረምራል ስለሚል ይህንኑ ለመስራት ም/ቤቱ ከአቋቋማቸዉ ቋሚ ኮሚቴዎች አንዱ የሆነው የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ከሚያከናዉናቸዉ ተግባራት አንዱ የአስፈፃሚውን እቅድና የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርትን በመገምገም ጥንካሬዎችንና እጥረቶችን በመለየት የላቀ አፈጻጸም ያላቸዉ ይበልጥ የሚጠናከሩበትን ዝቅተኛ አፈጻጸም ያላቸዉ ደግሞ የሚሻሻሉበትን አቅጣጫ በመስጠት አስፈጻሚዉ በዕቅድ ዘመኑ የያዙትን ግቦች እንዲሳኩና በዚህም አማካይነት ከሚመጣዉ ዕድገት የህ/ሰቡ ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ ነው፡፡

በዚህም መሰረት በኢፌዴሪ ሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የግብርና ሚ/ር እና የተጠሪ ተቋማት የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድን ከግብርና ዘርፉ ፖሊሲ እና የ10 ዓመቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ መነሻ በመገምገም በጥንካሬ እና በዕቅዱ ሊካተቱ የሚገቡ ቀሪ ጉዳዮችን በመለየት የሚከተለዉን ግብረ መልስ ሰጥቷል፡፡

2. ዓላማ

በሚንስትሩ እና ተጠሪ ተቋማት ላይ የ2014 ዕቅድ ዝግጅት በጥንካሬ እና በጉድለት የታዩትን ጉዳዮች በመለየት ግብረ-መልስ በመስጠት ውጤታማነትን ማረጋገጥ፡፡

3. ግቦች

- የተሰጡት ግብረ-መልሶች ሚከለሰዉ የዕቅድ አካል ተደርጎ እና ተስተካክሎ ለቋሚ ኮሚቴ በሪፖርት ቀርቧል፡፡
- በተቋሙ በጥንካሬ የተገመገሙ ነጥቦች ቀጣይነት ኖሯቸው እንደ እሴት ተወስዶ እና ለቀጣይ ስራዎች ማነሳሻ ሆነዋል፡፡

4. **2014 ዕቅድ ግብርናገተር ልማት ፖሊሲና ከ10 አመት መሪ ዕቅድ አንፃር የታዩበት አጠቃላይ ግምገማ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡**

4.1 ከፖሊሲ አንጻር

4.1.1 በጥንካሬ የታዩ ጉዳዮች

- የግብርና ገጠር ልማት ፖሊሲ ማሻሻያ ተዘጋጅቶ መቅረቡ፣
  - የ2014 ዕቅድ ላይ ሲዘጋጅ አጠቃላይ አገራዊ ነባራዊ ሁኔታን የፖሊሲ አቅጣጫ በመነሻ ሁኔታ ገምግሞ መነሳቱ፣
  - ለአ/አደሮች እና ለአርብቶ አደሮች የግብርና ቴክኖሎጂ ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡና የአርብቶ አደር ተጠቃሚነትን እንዲረጋገጥ የተሰራው ስራ ውጤታማ መሆኑ፣

4.1.2 መስተካከል የሚገባቸዉ ጉዳዮች

- የተዘጋጁው የግብርና ገጠር ልማት ፖሊሲ በሚኒስትሮች ም/ቤት ፀድቆ በፍጥነት ወደ ሥራ ማስገባት፤

4.2 ከ10 ዓመት መሪ ዕቅድ አንጻር

4.2.1 በጥንካሬ የታዩ ጉዳዮች

- የአስር አመት የግብርና ዕቅድ ከመንግስት አስር አመት መሪ ዕቅድ ጋር ዓላማዉ፣የትኩረት አቅጣጫ፤የማስፈፀሚያ ስልቶች የተናበቡ መሆናቸዉ፤
- የአስር አመት የግብርና ዕቅድ ከመንግስት የአስር አመት መሪ የልማት ዕቅድ ጋር የተጣጣመ መሆኑ፤
- አገራዊ አዝዕትና ሆርቲካልቸር ዝርያ ለማዳቀልመታቀዱ፣ግብርና መረጃ ስርዓት ለማዘመን በቴክኖሎጂ ለማስደገፍ መታቀዱ፣የገበያ ትስስር ለመፍጠር አቅርቦትና ፍላጎት መሰረት ተደርጎ መታቀዱ፤

4.2.2 መስተካከል የሚገባቸዉ ጉዳዮች

- በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የግብርና ዕቅድ ከልማት እቅድ ጋር ያልተጣጣመ ስለሆነ (ለአብነት፡-የበቆሎ ምርታማነት እና የማዳበሪያ አቅርቦት) መጣጣም አለበት፤
- 10 ዓመት ግብርና ሴክተር ዕቅድ ላይ የሰዉ ሀብት ልማት ግብ በግልጽ መቀመጥ አለበት፤

4.3 ከ2014 ዓ.ም ዕቅድ አንጻር

4.3.1 በጥንካሬ የታዩ ጉዳዮች

- በበጀት አመቱ በጀት ዓመት ገበያ ተኮር የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶ አደሮችና በሰፋፊ እርሻ በበልግ፣ በመኸር እና በበልግ መስኖ ለማልማት መታቀዱ፣

- በ2013 በጀት ዓመት የአፈፃፀም ውስንነቶችን በማሻሻል እና በአስር ዓመት ውስጥ የተቀመጡትን የማስፈፀሚያ ስልቶችን በአግባቡ ተግባራዊ ለማድረግ መታቀዱ፣
- በበጀት ዓመቱ የግብርና ግብዓትና ግብይትን ሰንሰለትን በማቀላጠፍ ምርታማነትን ሊያሳድጉ የሚችሉ ግብዓትን በመጠን፣ በዓይነት፣ በጥራት በወቅቱ ለአርሶ አደሩ ተደራሽ ለማድረግና በምርቱ የአገሪቱን የውጭ ምንዛሬ ገቢ ለማሳደግ የታቀደ መሆኑ፣
- ለዉጪ ገበያ የሚቀርቡ ጥራታቸዉን የጠበቁ አትክልትና ፍራፍሬዎች፣የቡና ምርት እንዲሁም ጤንነታቸዉ የተጠበቀ የቁም እንስሳትና ስጋ ምርት ወደ ዉጪ ለመላክ መታቀዱ፤
- የተፈጥሮ ሃብት ልማትን ለማስቀጠል የተጎዱ ቦታዎችን በመለየትና ከንክኪ ነፃ ሆነው እንዲለሙ በተለይ ለኀብረተሰቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለማድረግ እና ዘላቂ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሥርዓት ለማሻሻልና ለማጠናከር በተለይ ሴቶች ዘላቂ ጥቅም አግኝተው የተፈጥሮ ሃብትን ባለቤትነት ስሜት እንዲያለሙ በዕቅድ መያዙ፣
- የእንሰሳት ግብዓት ምርትና ጥራት ቁጥጥር ማሳደግ እንዲሁም የመድሃኒትና መኖ ህገ ወጥ ንግድና ሥርጭት ቁጥጥር ሥራ ማጎልበት በግቦችና በዝርዝር ተግባራት ተደግፈው መታቀዳቸው፡፡
- ለክልሎች አዳዲስ እና ነባር የእንስሳት መድሃኒትና መኖ አምራች፣ ጅምላ አከፋፋይ እና አስመጪ ድርጅቶች ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲያኙ እና እድሳት እንዲያደርጉ ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ መታቀዱ፤
- ከዉጭ አገር ያለቀላቸዉን ቴክኖሎጂዎች በማስመጣትና በማላመድ ቴክኖሎጂዎችን በፍጥነት ለማቅረብ በዕቅድ ዘመኑ 98 ቴክኖሎጂዎችን ለማላመድ መታቀዱ፣
- በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደሮች አካባቢዎች የሚሰሩ የምርምር ሥራዎች የእነዘህን አካባቢዎች ያላቸዉን የሰብል፣እንስሳትና የመኖ ችግርን ለመፍታት ታሳቢ ተደርጎ መታቀዱ፤
- የህብረት ስራ ማህበራት የድህረ እና ቅድመ ምርት ቴክኖሎጂዎች እንዲያቀርቡ መታቀዱ ፤

- በበጀት አመቱ የአቅም ግንባታ ለመስራት እና የኦዲት ግኝት ማስተካከያ በዕቅድ ውሰጥ ተዘርዝሮ መቀመጡ፣

4.3.2 መስተካከል የሚገባቸዉ ጉዳዮች

- የመስኖ ልማት ሥራዎች ግንባታን በተመለከተ 197 በማህበረስብ የሚተዳደሩ የመስኖ ተቋማት እና 157,157 በቤተሰብ የሚተዳደሩ ተቋማትን ለመንገባት መታቀዱ ጥሩ ሆኖ የበጀት ምንጭ እና የሚገነባበት ክልሎች ድርሻ ተለይቶ መቀመጥ አለበት፤
- የግበርና ባለስልጣን የ2014 ዓ.ም ዕቅድ በ2013 በጀት አመት የተደረሰበት አፈፃፀም በዝርዝር ገምግሞ መነሻነት ያደረገ አለመሆኑ በተጨማሪም የ10 አመት መሪ ዕቅድ እና ከዚሁ የሚቀዳውን የ5 አመቱ ዕቅድ መሰረት ማድረግ አለበት ፤ባለስልጣኑ ተቆጣጣሪ መ/ቤት እንደመሆኑ መጠን በቁጥጥር ሂደት የሚለያቸው ክፍተቶች እንዲስተካከሉ የሚውስዳቸው እርምጃዎችን በሚመለከት እቅዱ መታየት አለበት፣
- በግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የወጡትን አዳዲስ ዝርያዎችን ለአርሶ/አርብቶ አደሩ ተደራሽ ለማድረግ ከባለድርሻ አካላት ማለትም ከግብርና ኤክስቴንሽን፣ ከቴክኖሎጂ አባዥዎች እንዲሁም ከሌሎች ምርምር አካላት ጋር የተጠናከረ ቅንጅት ባለመኖሩ ቅንጅቱን ለማጠናከር የሚረዱ ስራዎችን በዕቅዱ ማካተት አለበት፤
- የምርምር ማዕከላት የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ላይ የተያዘዉ እቅድ ከችግሩ አንጻር ሲታይ ዝቅተኛ ስለሆነ ችግሩን ሙሉ ለሙሉ ለመፍታት በሚያስችል መልኩ መስተካከል አለበት ፤
- አለም አቀፍ ደረጃዉን የጠበቀ መዳኃኒት ማምረት እና ክትባት እና መዳኃኒት ለውጭ ገበያ ማቅረብ የሚለው ስትራተጅክ ግብ ላይ እንዲሁም ምርምር የሚደረግባቸው አዳድስ ምርቶች በመጠንና በቁጥር ምን ያህል እንደሆነ በሚመዘን መልኩ መቀመጥ አለበት፤
- ቡና ልማት ግባአት አቅርቦት ችግር(ፖሊባግ፣መጋዝ፣የቡና ማድረቂያ ወንፊት) እና የቡና እና ሻይ ምሩቅ የልማት ሰራተኞች እጥረት የሚፈታበት መንገድ በእቅድ ተይዞ መሰራት አለበት፤

- ኩታገጠም አመራረት ላይ የተጀመረዉ ስራ ጥሩ ሆኖ ከተደራሽነት አንጻር በሌሎች ክልሎች ያልተካተቱ መታየት አለበት ለአብነት፡-በቆሎ ምርት ላይ ቤንሻንጉል ጉሙዝ እና ጋምቤላ እንዲሁም የመካናይዜሽን ማዕከል ግንባታና የማሽን አቅርቦት ትኩረት ይሰጥበት፤
- የህብረት ስራ ማህበራት ጥራት እና ተጠቃሚነት ትኩረት ተሰጥቶት መሰራት አለበት፤
- የማህበረሰብ አቀፍ መድህኒት ዕዉቀቶች ላይ በማደራጀት እና እንዳይጠፉ እንዲሁም ብዝሀ-ህይወት እየጎዱ ያሉ አደገኛ እና ወረርሽኝ እጽዋት (ለአብነት፡-እንቦጭ፣የወያኔ ዛፍ) በእቅድ ተይዞ መሰራት አለበት፤

## 5. የትኩረት አቅጣጫ

- መደበኛና የበጋ ስንዴ መስኖ ልማት እና የቆላ ላይ መስኖ ልማት የተጀመረው ሃገራችንን ከተመጽዋችነት የሚያላቅቅ በመሆኑ ተጠናክሮ ይቀጥል፣
- የውጭ ምንዛሬ ለማስገኘት የቡና ልማትና ግብይት፣ የቁምና የእርድ እንስሳት ልማትና ግብይት፣ የእንስሳት ጤና አገልግሎት ተደራሽነት፣
- የበልግና የመኸር የግብርና ግብአቶች አቅርቦት በወቅቱና በጥራት እንዲቀርቡ እንዲደረግ ልዩ ትኩረት ቢሰጠው፣
- የበልግ እርሻ ማሣ ዝግጅትና የአርንጓዴ አሻራ ችግኝ ዝግጅትና የበጋ ተፋሰስ ልማት የሕዝብ ንቅናቄ ቅድመ ዝግጅት ሥራዎችና ትግበራ ትኩረት የበለጠ ተሰጥቶ ቢሰራ፣
- በድርቅና በጦርነት ጉዳት በደረሰባቸው አካባቢዎች ልዩ የማገገሚያ በተዘጋጀው ዕቅድ መሠረት በፍጥነት ወደ ተግባር ቢገባ፣
- ግብርናና ተጠሪ ተቋማት ባቀዳችሁት የሌብነትና ብልሹ አሰራር መታገያ ዕቅዳችሁ መሠረት የሕዝብ ሃብት እንዳይበላ ትግል ማድረግና የሕዝብን ተጠቃሚትማረጋገጥ፡፡ በሚኒስቴር መ/ቤቱና በተጠሪ ተቋማት በበጀት ዓመቱ የታቀደውን ተግባራት በብቃት ለመፈጸም ያስችል ዘንድ የሰው ኃይሉ በዕውቀት፣ በክህሎትና በአመለካከትና ዲሞክራሲ መርሆዎችና በሕብረ ብሔራዊ አንድነት አስተሳሰብ በመቅረጽ የብቃት ሥራ ትኩረት በመስጠት ለታሰበው ዕቅድ በማሳካት ሚናውን እንዲጫወት ማድረግ፡፡